

# ለትዳራችን ጥንካሬ ግንባታ፤ የትዳር ጓደኛዬና እኔ ምን ማድረግ አለብን?

በመጀመርያ ደረጃ፤ትዳራችሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ መሆኑን፤ ቀጥሎም አንዱ ለሌላዉ የተሰጠ ሊሆን እንደሚገባዉ ሁለታችሁም መገንዘብ አለባችሁ። ትዳራችሁን ከሚቦሮቡሩና ከሚሸረሽሩ ኃይላት ለመጠበቅ ከሁሉም የበለጠ የመከላከያ መሳሪያችሁ ሁለታችሁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላችሁ ጥልቅና ከፍተኛ የሆነ የጋራ ኅብረትና ለእግዚአብሔር ቃል ለመታዘዝ ያላችሁ መሰጠት ነዉ። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላችሁ ታማኝነትንና ታዛዥነትን የሚያሳየዉ እርምጃና ጉዞአችሁ፤ ከእንቅፋት ይጠብቃችኋል።

የሕያዉ አምላክ ቤተክርስትያን የእዉነት ዓምድና መሰረት እንደሆነች ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈዉ ደብዳቤ ላይ አሳስቡዋል (1 ጢሞ. 1፡15)። ስለእዚህም ነዉ አጥቢያ ቤትክርስትያናችን በእግዚአብሔር የጸጋና የምሕረት ሓይል ላይ በመደገፍ፤ እዉነት የሆነዉን የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ባለማቋዋረጥ ሳትሰለች ተልእኮዋን ከሚያዘናጋ ሁሉ ተለይታ፤ በጥንቃቄና በትጋት እየሰራች ያለችዉ።

በየሳምነቱ እሁድ በመደበኛዉ ስብሰባችን ላይ ከሚሰጠዉ ትምህርትና ስብከት ሌላ፤ በሰንበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ፤ በቤት ለቤት ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፤ በተለያዩ ኮንፍረንሶች፤ በተጋባዥ አስተማሪዎች፤ በድሕረ ገጽ አድራሻዋ፤ ወዘተ. የእግዚአብሔር ቃል ሳይቋዋረጥ ወደ እኛ ይመጣል። ወደእኛ የሚደርሰዉ ይህ የእግዚአብሔር ቃል በክርስቶስ ብቸኛ የማዳን ጸጋዉ ለተጠራነዉ ልጆቹ እንዴት መኖር እንደሚገባን ያስተምረናል (2ኛ ጢሚ. 3፡16)። እዉነቱን እንድናስታዉሰና በቃሉም መሰረት ልንኖር የሚያስችለንን ሀይል መቀበል እንድምንችል የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ቃል ገብቶልናል። ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እዉቀት እንድናድግ ያዘናል (2 ጴጥ. 3፡18)። ንግግራችን በጨዉ እንደተቀመመ እንዲሆን (ቆላስየስ 4፡6)፤ እንደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትህትና የተሞላንና ይቅረ ባይዎች እንድንሆን፤ እራሳችንን መግዛት የምንችልና በረጋ መንፈስ ሆነን ሌላዉን የምንገነባ (ኤፌ፣ 4፡29)፤ የምንሸካከም፤ የምንዋደድ፤ ባጠቃላይ የጌታችን ባህሪ አንጸባራቂዎች (ፊሊፐስዮስ 2፡5) እንድንሆን በየጊዜዉ በጋራም ሆነ



በግል የምናጠናዉ የእግዚአብሔር ቃል ያዘናል። ጌታ እንኳን ወዳጁንና ጎረቤቱን ቀርቶ፤ ጠላቶቹ እንኳዋ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ካፉ ክፉ ቃል አልወጣም (ኢሳ. 53፡7)። ታድያ አጠገባችን ቀንም ሆነ ማታ ላለዉ ወይም ላለችዉ የትዳር ወዳጃችን ከእኛ የክርስቶስ ባህሪ በትንሹ እንኳዋ ካልተንጸባረቀ የሩቅ ለሆነዉ እንዴት ይታየዉ? ከእግዚአብሔር ቃል ዉጪ ምን ያህል የተለየ ትምህርት ነዉ ለባልና ሚስት መልካም ግንኙነትና ትዳር ማዳበር የሚያስችል ምክር ሊኖር የሚቻለዉ?

ብዙ ጊዜ ባልና ሚስትን የሚያባላዉና ሰላማቸዉን የሚነሳዉ፤ ከእዚህም አልፎ የሚያፋታዉ ዋና ጉዳይ ገንዘብ መሆኑ በሀዘን የምንመለከተዉ ተደጋጋሚ ክስተት ነዉ። የክርስቶስ ትምህርት ተረስቶ የሰዉ ሕይወቱ በሀብቱ ብዛት እንደሆነ ተቆጥሮ (ሉቃ. 12፡ 13) ባልም ሆነ ሚስት ጥንቃቄን አጉድለዉ፣ ራሳቸዉን ሳይጠብቁ በስግብግብነታቸዉ በእግዚአብሔር ዓይን የከበረዉን ትዳራቸዉን ሲያፈርሱ፤ ልጆቻቸዉን ለክፉ ሲዳርጉ ለምን ልብ አይሰብርም፤ ለምንስ አያሳዝንም? እንደጌታችን ትእዛዝ ፍቅራቸዉ አንዱ ለሌላዉ መሆኑ ቀርቶ በገንዘብ ፍቅር (2ኛ ጢሞ. 6፡10) ዓይናቸዉ ታዉሮ አብሮ ያለዉን፣ አብራቸዉ ያለችዉን የትዳር ባልንጀራ ለመጉዳት ሲሩዋሩዋጡ ሲታይ ለምን አያስለቅስ?

ከመደበኛዉ የአጥቢያ ቤተክርስትያን ሳምንታዊ ትምህርቶችና ስብከቶች ሌላ በየሳምንቱ አርብ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ከሚሰበከዉ መልክት ሌላ፤ ትዳር ላይ ብቻ ያተኮረ ስብሰባዎች፣ ትምህርታዊ ዎረክሾፕ (ዓዉደ ጥናት) ቤተ ክርስትያን ታዘጋጃለች። በእነዚህ ልዩ ስብሰባዎችና ኅብረቶች ወቅትም በዋናነት የምንሰማዉ ያንኑ የእግዚአብሔርን ቃል ነዉ። ሰምተን ደግሞ ለቃሉ ታዛዥ ሆኖ መገኘቱ የእኛ ምርጫ ነዉ።

በትዳራችንም ቢሆን፤ በግልም ሆነ በኅብረታችን የሚከሰቱት ያለመግባባት ችግሮቻችን ዋና ምክንያት የምክር ማነስ፤ የትምህርት ማነስ፤ የስብሰባዎች ማነስ፤ ወዘተ. ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን የምንወስደዉ ያለመታዘዝ ምርጫችን ነዉ። ምርጫችን ደግሞ ሃላፊነትንና በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ህያዉ የሆነዉ የእግዚአብሔር ቃል ደጋግሞ ያሳስበናል (ማቴ. 12፡36፤ ሮሜ. 14፡12)።

የሚከተሉት ተግባራዊ የሆኑ መመርያዎችም በተለይ ትዳር ላይ ትኩረት በማድረግ ለትዳራችን መዳበርና መጠናከር ሊያግዙን ይችላሉ ተብለዉ ከእግዚአብሔር ቃል ተጨምቀዉ የቀረቡ ምክሮች ናቸዉ። ከታች የተዘረዘሩትን ምክሮች፤ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አመሳክረን በትህትናና በጥሞና አመዛዝን እዉነት የሆነዉን ለይተን በማየት፤ ለእግዚአብሔር መታዘዝን በመምረጥ ትዳራችንን መገንባት እንችላለን ብለን እናምናለን። ይህ ካልሆነ ግን፤ ካሁን በፊት እንደተሰበከዉ፤ በፊት ተጽፎ እንዳነበብነዉ፤ እንዳልተጠቀምንበት የሰዉ ከንቱ ልፋት ይሆናል፡፡ ምርጫዉ የኛዉ ነዉ። ከምርጫዉ ጋር ተከትሎ የሚመጣዉ ሀላፊነትና ተጠያቂነትም የእያንዳንዳችን ነዉ። ይህ ጽሑፍ ለበረከት እንዲሆን ጸሎታችን ነዉ።

**• ትኩረታችሁ ዉጫዊ ገጽታችሁ ላይ ሳይሆን ልባችሁ ላይ ይሁን።**

የሚበልጠዉ ዉስጣዊ ህይወታችሁ ነዉ እንጂ፤ዉጫዊ ገጽታችሁ አይደለም። የምሳሌዎች ጸሐፊ ይህንን እንዲህ ሲል በሚገባ ገልጾታል፡ “ዉበት ሀሰት ነዉ፤ ደም ግባት ከንቱ ነዉ፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች።” (ምሳ.31፡30)



ጴጥሮስ ይህንኑ የሚመስል መመርያ ለሚስቶች በ1ኛ ጴጥ. 3፡ 3-4 ላይ ሰጥቱዋል፤ ነገር ግን መመርያዉ ለባሎችም የሚዉል ነዉ፡- “ዉበታችሁ በዉጫዊ ነገሮች በመሽሞንሞን ይኸዉም ሹሩባ በመሰራት፤ በወርቅ በማጌጥና በልብስ አይሁን፤ ነገር ግን ዉበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋዉ እጅግ የከበረ፤ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፤ ምንጊዜም የማይጠፋ የዉስጥ ዉበት ይሁን።”

ትኩረታችሁ ለክርስቶስ ያላችሁን ፍቅር ማዳበር ከሆነ፤ ዉስጣዊ የሆነዉ ጥራት ያለዉ የእግዚአብሔርን መምሰል ባህሪያችሁ ሊያድግ፣ ሊዳብርና ትዳራችሁን ሊያጠናክር ይችላል።

**ትኩረታችሁ የትዳር ጉዋደኛችሁ እዉነተኛ ማንነት ላይ እንጂ፤ ሊሆን ወይንም ልትሆን ይገባታል ብላችሁ የምትመኙት እንከን የለሽ፤ ልበወለድ ወይንም አእምሮ የቀረጸዉ ሀሳብያዊ የትዳር ጉዋደኛ ማንነት ላይ መሆን የለበትም።**

ብዙ ትዳሮች ለመዉደቅ የሚንገዳገዱት አንዱ ሌላዉን ለማወቅ በቂ ጊዜ ካለመዉሰድ የተነሳ ብቻ ሆኖ ይታያል። የትዳር ባልንጀራችን፤ ተወዳጅ ቢሆንም ወይንም ብትሆንም፤ እንከን የለሽ ሊሆን ወይንም ልትሆን አትችልም። ለምን እንከን የለሽ አይደለም ወይንም አይደለችም ብለን የሙጥኝ ብለን ድርቅ ብንል፤ ትዳራችንን እንጎዳለን። ይህንን የተሳሳተ እዉንታዊ ያልሆነ ሀሳብ ትተን፡ ዛሬ በደረሱበት ቦታ ላይ እንዳሉ፡ በመቀበል የትዳር ባልንጀራችንን ለማወቅና ለመዉደድ ጥረት ማድረጉን እንጀምር። ይህንኑ ለማለት ነዉ ጴጥሮስ ባሎችን ከሚሰቶቻችሁ ጋር ስትኖሩ “በማስተዋል” ኑሩ ያላቸዉ። (1ኛ ጴጥ. 3፡7)

**የትዳር ባልንጀራህን መዉደድ ላይ ትኩረት መስጠት እንጂ፤ ለኔ የሚስማማኝ/የሚገጣጠመኝ ላይአይሁን።**

የትዳር ባልንጀራህ የፈለገዉን ይሁን ወይንም ትሁን፤ እርስ በእረስ መዋደድን መማር ይቻላል። ባብዛኛዉ በዓለም ላይ ገኖ እንደሚታመንበት ፍቅር እንዲሁ የሚከሰት ዱብ ዕዳ፤ ጥሎብኝ የሚባል፤ እንደደራሽ ዉሃ እየጋለበ የሚየሰጥመን ሳይሆን፤በተቃራኒዉ፤ ለመዉደድ ምርጫ ማድረግ የምንችለዉ ነገር ነዉ። ለእዚህም ነዉ ጳዉሎስ ባሎች ሚስቶቻቸዉን እንዲወዱ ሲያዝ (ኤፌ. 5፡25) እንዲሁም ሚስቶች ባሎቻቸዉን እንዲወዱ የሚያዘዉ (ቲቶ 2፡4)። የእግዚአብሔር ቃል በትዳር ያሉ አባላት “ይገጣጠሙ” ይሆን፤ “ይጣጣሙ" ይሆን የሚለዉ ግምገማ ላይ ስሌት ሲያሰላ አናገኝም። እግዚአብሔር ሁለቱም፤ ባልና ሚስት እርስ በእርስ እንዲዋደዱ ያዛል።



# የባለትዳሮች ኅብረት አገልግሎት

የባለትዳሮች ኅብረት አገልግሎት በኢትዮጵያዉያን ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስትያን አስተዳደር መመሪያና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት፤ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አካል ሆኖ የሚሰራ ነዉ ። ዋና የአገልግሎቱ ትኩረት ባልና ሚስት እርስ በእርስ ሊኖራቸዉ የሚገባዉን ግንኙነት በእግዚአብሔር ቃል መሰረት በፍቅር፤ በመከባበርና አንዱ ሌላዉን ለመረዳት (to understand each other) በመጣርና በመተሳሰብ ፤ በመደጋገፍ ላይ እንዲመሰረትና እንዲያድግ ማበረታታት ነዉ ።

አገልግሎቱ አጥቢያ ቤተክርስተያኒቱ የተሰጣትን ዋና የማስተማር ተልእኮዋን ቤተሰብን በተመለከተ መስክ (topics/subject) ረገድ ለመተካት ሳይሆን፤ ስራዋን በማገዝና በመደገፍ እንደ አንድ የአካልዋ ክፍል ለተልኮዋ ስኬት መተባበር ነዉ ።

አገልግሎቱ በተለይ የታወቀበትና በየዓመቱ በጉጉት በብዙዎች ዘንድ የሚጠበቀዉ ‘በፌበሪዎሪ’ አጋማሽ ላይ የሚ ኪያሄደዉ “የፍቅረኞች ጊዜ” ነዉ ። በዚህ ጊዜ ባለትዳሮች በሚኖራቸው የኅብረት ጊዜ ትዳርን በተመለከተ የተለያዩ ትምህርቶች ይሰጣቸዋል።

እንደዚሁም በየጊዜው ባለትዳሮችን በተመለከተ፥ ትምህርታዊ አውደ ጥናቶችን (workshops) በማዘጋጀት፤ በቤተሰብ ነክ ጉዳዮች ላይ እግዚአብሔርን በማገልገል የተሰማሩትን ወንድሞችና እህቶችን ከዉጪም ሆነ ከዉስጥ በመጋበዝ የማነቃቂያና የማበረታቻ ፕሮግራሞችን ያስተባብራል ።